THE ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION
AFRICAN CLEAN CITIES PLATFORM
UN-HABITAT
WASTE WISE CITIES
Urban Pathways
IKI INTERNATIONAL CLIMATE INITIATIVE


# የእኔ ቆሻሻ፣ የሁላችንም ሀብት !


የመፍትሄው አካል ይሁኑ!




ልጄ እባክህ ይህንን ቆሻሻ ለይተህ አስቀምጥ። በነገው ዕለት ቆሻሻ ከየቤቱ የሚሰበስቡ ማህበራት ይመጣሉ::
ሁሉንም ነገር በአንድ ማጠራቀሚያ ማስቀመጥ አይቻልም? ለምን መለየት አስፈለገ?


ይህ በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው። ቆሻሻችንን ከለየን እንደገና ጥቅም ላይ ለማዋል ይቀለናል። በዚህም ውድ የሆኑ ሀብቶቻችንን ከብክነት ለማዳን ከማስቻሉም በላይ አዳዲስ ጠቃሚ ነገሮችን ለማግኘት ይረዳናል።
እውነት? ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?
ምን መሰለህ ... ከምናመነጫቸው ቆሻሻዎች እንደ ፕላስቲክ፣ ወረቀት፣ ብርጭቆ እና የመሳሰሉትን ከምግብ ተረፈ ምርቶች ለይተን ካስቀመጥናቸው ፣ መልሶ ለመጠቀም ቀላል ይሆናሉ ስለዚህ ወደ ሌሎች አዳዲስ እቃዎች ለመለወጥ ይረዳናል።


ለምሳሌ የምግብ ተረፈ ምርቶችን ለብቻ ከለየን ወደ ተፈጥሮ ማዳበሪያ፣ ባዮጋዝ ወይም የኤሌክትሪክ ኃይል መለወጥ ይቻላል።
ቆሻሻን መለየት የስራ ዕድል ይፈጥራል ፤ የገቢ ምንጭም ይሆናል !
ቆሻሻን በመለየት ንጹሕ ኃይል ማመንጨትም ያስችለናል !


እሺ...
ግን ቆሻሻ ባይለይ
ምን ይሆናል ?
ያልተለየ ቆሻሻ ወደ
ማስወገጃ ቦታ ሲደርስ
አካባቢን (ውሃን፣
አፈርን እና አየርን)
ይበክላል ።
ስለዚህ ለመኖር
የሚያስፈልገንን ምግብ፣
ውሃ እና አየር
እንድናገኝ፤
የአካባቢያችንን
ጤንነት መጠበቅ
ኣስፈላጊ ነው።
ያለ ምግብ እና ውሃ መኖር
አልችልም::
ስለዚህ አካባቢዬን መጠበቅ
እፈልጋለሁ! ሌላ ምን
ማድረግ እችላለሁ?


በትምህርት ቤቴ ውስጥ ስለ 5ቱ የ “መ” መርሆች ማለትም ማጤን፣ መከላከል፣ መቀነስ፣ መልሶ መጠቀም፣ እና ኡደት ማድረግ በተመለከተ በሚገባ ተምሬአለሁ::



ቆም ብለን እናስብ !
አብዛኞቹ ሳናስተውል የትም የምንጥላቸው ቆሻሻዎች በአግባቡ ከተያዙ ሀብት ናቸው::





ይህን የውሃ ጠርሙስ መልሰን መላልሰን ለውሃ መያዣነት መጠቀም እንችላለን ወይም ለይተን የቆሻሻ ቅርጫት ውስጥ ብናስቀመጠው እንደገና ጥቅም ላይ ለማዋል የሚሰሩ ኩባንያዎች አዲስ ብርጭቆ ለመስራት ያገለግላቸዋል።




ሌላው ልታደርግ የሚገባህ አስፈላጊ ነገር ደግሞ አንድ ጊዜ ብቻ ተጠቅመን የምንጥላቸውን ዕቃዎች አለመጠቀም ነው።




እነዚህ ዕቃዎች የምንጠቀመው በአብዛኛው ጊዜ ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ሲሆን ከዚያም እናስወግዳቸዋለን፡፡ ለምሳሌ ለአትክልት እና ፍራፍሬ መያዣ የሚሆኑ የፕላስቲክ ውጤቶች ወዘተ






አ፣ አሁን ተረድቻለሁ ።
ምግብ ለመግዛት በሄድን ቁጥር እነዚህን
የፕላስቲክ መያዣ ከረጢቶች አያለሁ። አስቤዛ
ወደ ቤት ለማድረስ ብቻ እንጠቀምባቸዋለን ፤
ከዚያም እንጥላቸዋለን ።
በሚቀጥለው ጊዜ እንደገና ጥቅም
ላይ ሊውሉ የሚችሉ ቦርሣዎችን ወይም
ዘንቢሎችን ይዘን ብንሄድ እነዚህን
ቆሻሻዎች አናመነጭም ።


**መልሶ መጠቀም** የተፈጥሮ ሀብትን
ለመቆጠብና አካባቢያችን ከአደጋ
ለመጠበቅ ይረዳል። ለምሳሌ ያህል፣ ከእናንተ
የሚበልጡ የዘመዶቻችሁ ልጆች የጠበባቸዉን
ልብሶች ሲሰጧችሁ...
እናንተም የማትጠቀሙባቸዉን መጻሕፍት ወይም
መጫወቻዎች እንደ ስጦታ መስጠት ትችላላችሁ።
ለጓደኞቻችሁ፣
ለቤተሰቦቻችሁ እና ለፕላኔታችሁ ለጋስ ሁኑ!


አንዳንድ ጊዜ  አዳዲስ ነገሮች ባያስፈልጉንም እንኳ እንፈልጋለን ።
ምንም ነገር ከመግዛታችን በፊት ቆም  ብለን ማሰብ ይኖርብናል
ቆሻሻን ለመቆጣጠር በጣም ውጤታማው መንገድ መጀመሪያውኑም አለማመንጨት ነው! በዚህ መንገድ ቆሻሻን መቀነስ እንችላለን።
ስለ መጨረሻው “መ” ስ ?
እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል! ቲሸርትህን ተመልከት፡ ከአሮጌ የፕላስቲክ ጠርሙሶች እንደተሰራ ታውቃለህ?
ቴክኖሎጂዎች እና አዳዲስ ፈጠራዎች አካባቢያችንን ለመጠበቅ ሊረዱን ይችላሉ!


ተመልከች
5ቱን የ“መ” መርሆዎች
በመጠቀም ምን ያህል ቆሻሻ
እንደቀነስን !
አሁን ይህ
ቆሻሻ ብቻ ነው ወደ ደረቅ
ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ የሚሄደዉ...
የተቀረዉ ተመልሶ ጥቅም
እንዲሰጥ ይደረጋል ።
ወረቀት
ፕላስቲክ
ብርጭቆ
ብረት
የሚበሰብሱ


አንድ አባባል አለ። ቆሻሻን ባንቀሳቅል፣ የሚጠቅሙንን ሀብቶች ብንለይ፤ የምናመነጨውን ቆሻሻ እንቀንሳለን፤ ሀብቶቻችንን እናድናለን፤ ጥሬ ዕቃም እናገኛለን፡፡ ስለዚህ ቆሻሻን በአግባቡ መለየት ይገባናል!
አምስቱን የ “መ” መርሆዎች በመጠቀም አካባቢዬን ለመጠበቅ እንዲሁም ለማኅበረሰቤ ሀብት ለመፍጠር እሞክራለሁ! አሁንም ቆሻሻ ሲኖረኝ በአግባቡና በትክክለኛ ቦታ መቀመጡን አረጋግጣለሁ፡፡
ማለፍያ!
ሁሉም ሰው ቆሻሻን ያመነጫል፣ ስለዚህ ሁሉም ሰው ለዚህ ጉዳይ ኃላፊነት አለበት እና ሁሉም ሰው ከዚህ ጥቅም ማግኘት ይችላል!


ወዴት እየሮጥክ ነው?
ለጓደኞቼ ስለ 5ቱ የ “መ” መርሆች መንገር እፈልጋለሁ። አንድ ላይ ስንተባበር የተሻለ ነገር ማሳካት እንችላለን።
የጽዳት ጀግና



የበለጠ መረጃ ለማግኘት በከተሞችዎ እና በማህበረሰብ ውስጥ የቆሻሻ አያያዝን ለማሻሻል እንዴት እርምጃ መውሰድ እንደሚችሉ ይጎብኙን

በ

https://unhabitat.org/waste-wise-cities

https://africancleancities.org

## የእርስዎን የንቃተ-ህሊና እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልቶችን እና ልምድዎን

- ምን ውጤት አስገኝተዋል?
- የትኞቹ ተግዳሮቶች አጋጥሞዎታል?
- ምን መፍትሄ ሰጡ?



## ያጋሩን

WASTEWISECITIES@UN.ORG

ACCP@UN.ORG

Addis Ababa Cleansing Management Agency UN-Habitat Ethiopia

UNHabitat_ETH

Urban Pathways

IKI INTERNATIONAL CLIMATE INITIATIVE

THE ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION

AFRICAN CLEAN CITIES PLATFORM PLATE-FORME AFRICAINE DES VILLES PROPRES

UN-HABITAT

WASTE WISE CITIES